# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር-232313

ጥቅምት 05 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ኤልሳቤጥ መኩሪያ ተወካይ ትዕግስት ገበየሁ - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሳምራዊት መሐመድ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ ንብረትነቱ ብቸኛ ወራሽ የሆንኩላት የእናቴ የወ/ሮ አይሻ አብደላ ሆኖ በስሟ ተመዝግቦ በአዲስ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የሚገኝ መኖሪያ ቤትና ይዞታ በህገ ወጥ መንገድ በውርስ ወደ አመልካች የተላለፈ በመሆኑ የሟች እናቴ የውርስ ሐብት የሆነው የቤት ቁጥር 415 በውርስ አጣሪ ተጣርቶ እንዲወሰንልኝ በማለት የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ክርክር የተነሳበት የቤት ቁ.415 ሟች ወ/ሮ በለጡ መኩሪያ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ቀበሌ 09 በውርስ መንግስት በወሰደባቸው የግል ቤት በምትክነት የተሰጣቸውና ለ40 ዓመት ሲጠቀሙበት የነበረ ቤት ነው፡፡ ክርክር ያስነሳው ቤት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠኝ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሕገወጥ መንገድ ሳይሆን በሕግ አግባብ ወ/ሮ በለጡ መኩሪያን በመውረስ በመሆኑ የውርስ ሃብቱ ተጣርቶ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት ተጣርቶ በቀረበው የዉርስ ሪፓርት ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር እና በፍ/ቤት የቀረቡ ማስረጃዎችን በመመርመር የቤት ቁጥር 415 የሆነው ቤት የሚች ወ/ሮ አይሻ አብደላ የግል ሐብት ስለሆነ ቤቱ የስር አመልካች የውርስ ሐብት ነው በማለት የውርስ አጣሪ ሪፖርት በማፅደቅ ወሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች የቤት ቁ.415 የሚች ወ/ሮ አይሻ አብደላ የግል ሃብት ስለሆነ ቤቱ የውርስ ሐብት ነው መባሉን በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337(1) መሰረት ተሰርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፤ አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በተጠሪ ወላጅ እናት ስም በ1956 ዓ.ም ተመዝግቦ የነበረ ቢሆንም በ1967 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የከተማ ቤት መመዝገቢያና መረከቢያ ቅጽ 003 ተመዝግቦ በመንግስት የተወረሰ ነዉ፡፡ የአመልካች ወላጅ እናት ወ/ሮ በለጠ መኩሪያ በቤቱ የቤት ኪራይ እየከፈሉ ቆይተዉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አመልካች ወራሽነቴን አረጋግጬ ለእናቴ በማካካሻነት የተሰጠዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በዉርስ ተላልፎልኝ በስሜ ካርታ ተዘጋጅቶ ተሰጥቶኛል፡፡ የሚመለከተዉ አካልም ተጠይቆ ስመ ሀብቱ ቤቱ ለአመልካች እናት የተላለፈዉ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት መሆኑን ጠቅሶ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ቤቱ የአመልካች እናት ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ በማካካሻነት ተሰጥቶአቸዉ ሲኖሩበት ቆይተዋል፡፡ የተጠሪ ወላጅ እናት ሟች ወ/ሮ አይሻ አብደላ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የትርፍ ቤት መመዝገቢያ ቅፅ 003 ላይ ተመዝግቦ እያለ እና የቤ/ቁጥር 057 በመባል በወቅቱ የሚታወቅ ቤት ዉስጥ አንድ ክፍል ቤት ብቻ ተለይቶ መንግስት እንደወረሰዉ እና ብዙ ክፍሎች ያሉት ቤት እንዳልተወረሰ አድርጎ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የገለጸዉ ተገቢነት የለዉም፡፡ በአጠቃላይ እናታቸዉ በህግ ያጡትን መብት ተጠሪ በወራሽነት እንዲያገኙ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ታርሞ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም በዚህ ጉዳይ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬ ነገርና የተሰጠው ውሳኔ የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ፣ ተጠሪ ታህሳስ 07 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት መልስ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤ/ቁጥር 415 የሆነዉ ቤት ወላጅ እናቴ በማካካሻ ተሰጥቶአቸዉ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ እርሳቸዉ ከሞቱ በኋላ በዉርስ ተላልፎልኝ በስሜ ተመዝግቧል በማለት ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩላቸዉ ቤቱ በሟች እናቴ ወ/ሮ አይሻ አብደላ ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ እና በመንግስትም ያልተወረሰ መሆኑን ጠቅሰዉ የሚከራከሩ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቤቱን ሁኔታ አስመልክቶ የሚመለከታቸዉ የአስተዳደር አካላት እንዲያጣሩ ያደረገ ሲሆን በዚህም መሠረት የአዲስ

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከተማ ክ/ከተማ ቤቱ ከ1956 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ በተጠሪ እናት ወ/ሮ አይሻ አብደላ ስም ተመዝግቦ እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ በስማቸዉ ግብር ሲከፈልበት እንደነበረ፣ የሟች ወ/ሮ በለጠ መኩሪያ የኑዛዜ ወራሽ ናቸዉ በሚል መጋቢት 27 ቀን 2004 ዓ.ም ቤቱ በአመልካች ስም መመዝገቡን የሚያሳይ ምላሽ መስጠቱን፤ እንዲሁም የቀድሞ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በ1956 ዓ.ም ከወ/ሮ አፀደ ስዩም ወደ ወ/ሮ አይሻ አብደላ (የተጠሪ እናት) በግዥ ስጦታ የተላለፈላቸዉ መሆኑን የካርታ ቁጥር 44798 እንደሚያሳይ፣ ሟች ወ/ሮ በለጡ መኩሪያ በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ያልነበረዉና ስመ ሀብቱ በአመልካች ስም እንዲሆን የተደረገዉ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ እንጂ ከህግ ወይም ከዉል በመነጨ መብት አለመሆኑን፣ ቤቱ ለወ/ሮ በለጡ መኩሪያ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት በማካካሻነት የተሰጣቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ምንም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑንም ፍርድ ቤቱ በእራሱ ባደረገዉ ማጣራት ማረጋገጡን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

ፍርድ ቤቱ የአመልካች አዉራሽ ወ/ሮ በለጡ መኩሪያ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤት ላይ የባለቤትነት መብት እንደሌላቸዉ እና ለማካካሸነት ከመንግስት የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በሚል የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ ሲሰጥም ከላይ በተመለከተዉ አግባብ ከሚመለከታቸዉ አካላት የቀረቡለትን እንዲሁም እራሱ በተለያየ መንገድ ባደረጋቸዉ ማጣሪያዎች የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ነዉ፡፡ በመሠረቱ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ በትዕዛዝ በጸናዉ ዉሳኔ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 89176 ላይ ታህሳስ 26 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 282871 ላይ ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ይህ ችሎት ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም